Tularemia

Amharic



# ቱላሪሚያ

## ቱላሪሚያ ምንድነው?

ቱላሪሚያ ብርቱና በጣም ሊቆስል በሚችል ዓይነት ረቂቃን ነፍሳት ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው። ረቂቃን ነፍሳቱ ጭድ፣ ውሃ፣ አፈር ወይም የእንስሳ ሬሳ ውስጥ ለረጅም ሳምንታት በሕይወት መቆየት ይችላሉ።



*መዥገሮች የቱላሪሚያ ረቂቃን ነፍሳትን ሊሸከሙ ይችላሉ*

የቱላሪሚያ ምልክቶች ለበሽታው እንደተጋለጡበት ዓይነት መንገድ ሊለያዩ ይችላሉ። ምልክቶቹ የቆዳ የቁላ ቁስል፣ ያበጡና የሚያሙ እጢዎች፣ የተቆጡ ዓይኖች፣ የጉሮሮ ሕመም፣ የአፍ ውስጥ ቁስሎች ወይም የሳንባ ምች መስለው ሊታዩ ይችላሉ። ረቂቃን ነፍሳቱን ወደ ውስጥ ከተነፈሱት ምልክቶቹ ድንገት የሚመጣ ትኩሳት፣ ብርድ ብርድ የማለት ስሜት፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ሕመም፣ የመጋጠሚያ ሕመም፣ ደረቅ ሳልና እየባሰ የሚሄድ ድካም ናቸው። ቱላሪሚያ የሳንባ ምች ካስከተለ የደረት ሕመም፣ የደም መውጣት፣ የመተንፈስ ችግር ወይም የመተንፈስ ማቆም ሊያስከትል ይችላል።

አብዛኛውን ጊዜ ምልክቶች የሚታዩት ለበሽታው ከተጋለጡ ከሶስት እስከ አምስት ቀን በኋላ ሲሆን አንዳንዴ ግን ከተጋለጡ ከአንድ እስከ 14 ቀን በኋላም ሊታዩ ይችላሉ።

በአንቲባዮቲክ ካልታከሙ በስተቀር የሳንባ በሽታ ወይም ባጠቃላይ የቱላሪሚያ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ኃይለኛ አደጋ ላይ ናቸው። ሕክምና ካላገኙ ግን ይህን ዓይነት በሽታ ከያዛቸው ሰዎች ውስጥ ከ30 እስከ 60 በመቶ የሚሆኑት ሊሞቱ ይችላሉ።

በአገር ውስጥ በአጠቃላይ በዓመት ወደ 200 ሰዎች በተፈጥሮ በሚመጡ መንገዶች ቱላሪሚያ ይይዛቸዋል - ይህ የሚከሰተው በአብዛኛው በምዕራብና በመካከለኛው ደቡብ አሜሪካ ውስጥ ነው። በአለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ በሚኔሶታ ውስጥ አምስት በሽተኞች ተገኝተዋል።

## ቱላሪሚያ የሚይዘው እንዴት ነው?

ቱላሪሚያ በቀላሉ ሊይዝ ይችላል - ለማሳመም ከ10 እስከ 50 ረቂቃን ነፍሳት በቂ ናቸው። በተፈጥሮ ረቂቃን ነፍሳቱን ተሸካሚ የሆኑት እንስሶች የአይጥ ዘሮች፣ ሽኮኮዎችና ጥንቸሎች ናቸው።

ሰዎች ሊይዛቸው የሚችለው፦

- ከመዥገር፣ ከሚናከሱ ዝንቦችና ከሌሎች ነፍሳቶች ንክሻ
- በሽታው ያለባቸውን እንስሶች ወይም የእንስሳ ሬሳ ከመንካት
- የተበከለ ምግብ ከመብላት፣ የተበከለ ውሃ ከመጠጣት ወይም የተበከለ አፈር ከመንካት
- ቤተ ሙከራ ውስጥ ወይም ተመሳሳይ ቦታ ውስጥ ረቂቃን ነፍሳቱን በአየር ወደ ውስጥ በመተንፈስ

ቱላሪሚያን እንደ ጦር መሣሪያ መጠቀም የሚቻልበት መንገድ ብዙ ሰው ባለበት ቦታ ውስጥ አየር ላይ በመልቀቅ ይሆናል።

## ከሌላ ሰው ሊይዝ ይችላል?

በሽታው ከሰው ወደ ሰው የተላለፈበት ሁኔታ እስከ ዛሬ ድረስ አይታወቅም። ረቂቃን ነፍሳቱ አንዴ አየር ውስጥ ከተለቀቁ በኋላ በበሽታው መያዝ መቀጠል የሚቻል አይደለም። ረቂቃን ነፍሳቱ አንድ ጊዜ አየር ላይ ከተለቀቁ በኋላ ለረጅም ጊዜ በሕይወት መቆየት እንደማይችሉ ይታመናል።

MINNESOTA MDH DEPARTMENT OF HEALTH
Communications Office
625 North Robert Street/Box 64975
St. Paul, MN 55164-0975
(651) 201-4989
www.health.state.mn.us

## የሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚታመነው ለምንድነው?

ይህንን ለማድረግ ከባድ ቢሆንም ብዙ ሰው ባለበት ቦታ ውስጥ ቱላሪሚያን አየር ላይ መልቀቅ ኃይለኛ የሽብር መሣሪያ ሊሆን ይችላል። የቱላሪሚያ ጥቃት ሲኖር የመጀመሪያ ምልክቱ ከሶስት እስከ አምስት ቀኖች በኋላ ብዙ ሰዎች ሕክምና ሲፈልጉ ይታያል። የአንቲባዮቲክ ሕክምና ካላገኙ ብዙ ሰዎች ሊሞቱ ይችላሉ።

የ World Health Organization (WHO) እንደዘገበው አምስት ሚሊዮን ሕዝብ የሚገኝበት ከተማ ውስጥ አየሩ ላይ 50 ኪሎግራም (ማለትም 110 ፓውንድ) የሚሆን የቱላሪሚያ ረቂቃን ነፍሳት ቢበተን በጣም ከባድ ችግሮች ይፈጥራል። ይህ ዓይነት ጥቃት ቢከሰት 250 ሺህ ሰዎች በጠና እንደሚታመሙና 19 ሺህ ሰዎች እንደሚሞቱ WHO ያምናል።

የU.S. Centers for Disease Control and Prevention (CDC) እንደ ሽብር መፍጠሪያ መሣሪያ ለመጠቀም የሚያስችል ባሕርዮች ናቸው ከሚለው ውስጥ ብዙውን ቱላሪሚያ ይዞ ይገኛል፥

- ከሰው ወደ ሰው ባይተላለፍም በቀላሉ ማዛመት ይቻላል።
- በሰው ጤንነት ላይ እስከ ብዙ ሞት የሚያስከትል ሰፊ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል።
- ሰፊ ሽብርና ማኅበራዊ ሁከት ሊፈጥር ይችላል።
- ለቱላሪሚያ ጥቃት ለመዘጋጀት ልዩ ዓይነት እርምጃዎች አስፈላጊ ናቸው።

## ሊታከም ይችላል?

በመተንፈስ በገባ ቱላሪሚያ ምክንያት የሚመጣን የሳንባ በሽታና አጠቃላይ ሕመም በአንቲባዮቲክ ማከም ይቻላል። ሕክምና ካላገኙ ይህን ዓይነት በሽታ ከያዛቸው ሰዎች ከ30 እስከ 60 በመቶው ሊሞቱ ይችላሉ። ሕክምና ካገኙ ግን በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካን አገር ውስጥ በበሽታው የመሞት ዕድሉ ከሁለት በመቶ ያነሰ ነው።

## ከበሽታው መከላከል ይቻላል?

በአሁኑ ጊዜ ለሰፊው ሕዝብ የሚሰጥ ክትባት የለም። የ U.S. Food and Drug Administration በአሁኑ ጊዜ ለሙከራ ቤት ሠራተኞች የሚሆን ክትባት በመፈተን ላይ ይገኛል።

## ለቱላሪሚያ የተጋለጥኩ ከመሰለኝ ምን ማድረግ አለብኝ?

ለቱላሪሚያ መጋለጥዎን ማወቅ መቻልዎ አዳጋች ነው። ሆኖም ሐሳብ ከያዝዎት ዶክተርዎን ያነጋግሩት። በአካባቢዎ ጥርጣሬ የሚያሳድር እንቅስቃሴ ካዩ - ማለትም የበሽታውን ጀርሞች እንደ ጦር መሣሪያ ለመጠቀም የሚሞክር ካዩ - በአካባቢዎ ለሚገኘው የሕግ አስከባሪ ድርጅት ያሳውቁ።